# HARAMAYA UNIVERSITY VETERINARY MEDICINE STUDENTS

## በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የእንስሳት ህክምና ኮሌጅ ተማሪዎች

ቀን----------------------------------

ሐረማያ

ጉዳዩ፡- <u>ቅሬታ ማቅረብ ይመለከታል፡፡</u>

የ ኮሮና ቫይረስ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጤና ስጋት መሆኑ ይታወቃል፡፡በአሁኑ ጊዜ የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከልና ለመግታት መንግስት መጠነ ሰፊ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡የዓለም የጤና ድርጅትም በሽታው ወረርሽኝ መሆኑን ካወጀበት ጊዜ አንስቶ ለጥንቃቄ ይጠቅማሉ ብሎ ካስቀመጣቸው መፍትሄዎች መካከል የሰዎች መሰባሰብን የሚሹ ጉዳዮችን ማስቀረት በዋናነት ይገኝበታል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የመጡ በመኾናቸው ተቋማቱን ዘግቶ ተማሪዎቹን ወደ የቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ ማድረጉ ቫይረሱ እንዳይስፋፋ ስለሚያደርግ ተቋማቱ ተዘግተዋል። ስለሆነም ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በወረሽኙ መስፋፋት ስጋት ምክንያት በኮቪድ-19 ለተጠረጠሩ ለይቶ ማቆያነት እና ለቫይረሱ ናሙና መመርመሪያነት እና ሌሎች ማንኛውንም ቫይረሱን ለ መግታት አጋዥ የሆኑ ነገሮችን በማድረግ ሕብረተሰቡን እያገለገለ ይገኛል ። ይህ ሁኖ ሳለ የኮቪድ-19 ስጋት ሳይጠፋ ለተመራቂ የእንስሳት ህክምና ተማሪዎች የመመረቂያ ምርምርና የተግባር ልምምድ (Farm, laboratory, abattoir, Clinical experiences )አጠናቀን ለፈተና እና ምርቃት እንድንዘጋጅ እየተነገረን ነው ።

ነገር ግን በዚህ ከባድ ጊዜ ለኛ የእንስሳት ህክምና ተማሪዎች የመመረቂያ ምርምርና የተግባር ልምምድ(Farm, laboratory, abattoir, Clinical experiences)አጠናቀን ለፈተና እና ምርቃት ለመዘጋጀት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከባድ ነው ።

1ኛ. ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ተቋማቱን ዘግቶ ተማሪዎችን ወደ የቤተሰቦቻቸው እንደመለሱ ይታወቃል ስለሆነም የመመረቂያ ምርምርና የተግባር ልምምድ ስንሰራባቸው ወደ ነበሩት ቦታች ተመልሰን ማከናወን ለቫይረሱ ተጋላጭነትን ይጨምርብናል ።

2ኛ.እንደሚታወቀው ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በኮቪድ-19 ለተጠረጠሩ ለይቶ ማቆያነት እና ለቫይረሱ ናሙና መመርመሪያነት እያገለገለ ይገኛል፣ ይህም ቦታው ለቫይረሱ ከፍተኛ ተጋላጭ እንደሆነ ይታመናል።

Email address: -------------------@gmail.com የመልስደብዳቤዎትንበ Email አድራሻችንመላክይችላሉ።
phone no. 0906698454

3ኛ. ለቫይረሱ ተጋለጭ ከሚያደርጉት መካከል ከእንስሳት ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት እንደሆነ ይታወቅል ይህም ስራችንን እንዳንጨርስ እጅግ ከባድ እንደሚያደርገው እርግጥ ነው።

4ኛ. ይህን አይነቱ ወሳኝ መረጃ በኮሌጅ እና በዩኒቨርሲቲው ድህረ-ገፁ ሳይገለፁ ጥቂት ተማሪችን በማሳመን ይህን ብዙሃኑን ያላማከለ ውሳኔ ድጋሚ እንዲመለከትልን።

ስለሆነም ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ከላይ የቀረቡ መሠረታዊ የተማሪዎችን ጥያቄ ተመልክቶ የመመረቂያ ግዜውን የኮቪድ19 ስጋት በተወገደበት ጊዜ ጤንነታችንን እንዳይጎዳ እና ነገን ማየት እንድንችል ዩኒቨርሲቲው ጉዳዩን አይቶት ምላሽ እንዲሰጠን እንጠይቃለን።

ከሰላምታጋር

Email address: -------------------@gmail.com የመልስደብዳቤዎትንበ Email አድራሻችንመላክይችላሉ።
phone no. 0906698454